# ”ዘይተቐልዐ ታሪክ ህዘቢ ኢሮብ” ሲዳሰስ

ክፍል ሁለት

## እውነት በኢሮብ ወረዳ ዴሞክራሲያዊ የራስ አስተዳደር ተመስረቷል?

ከበየነ ገብራይ

በክፍል አንድ መግቢያዬ ላይ እንዳስቀመጥኩት ”ዘይተቐልዐ ታሪክ ህዚቢ ኢሮብ” በሚል ርእስ በቪዲዮ ተቀርጾ በአቶ ጸጋው ታደሰ በተተረከው የኢሮብ ህዝብ ታሪክ ውስጥ ከእውነተኛ ታሪክነት ይልቅ የአንድ የፖለቲካ ድርጅት ፕሮፓጋንዳ፣ እምነትና ፍላጎት ይበልጥ የተንፀባረቀባቸው ነጥቦች ናቸው ብዬ የማምንባቸውን ከታሪኩ በመጥቀስ እንደምተችባቸው ቃል በገባሁት መሰረት ክፍል ሁለትን የኸው ለዛሬ ይዤ ቀርቤያለሁ። በዚህ መሠረትም በዛሬው መጣጥፌ የምመለከተው ”ዘይተቐልዐ ታሪክ ህዝቢ ኢሮብ” በሚለው ዶክመንታሪ ፊልም ውስጥ ዛሬ በኢሮብ ወረዳ ተመስርቷል ተብሎ ስለሚተረከው ”ዴሞክራሲያዊ የውስጥ አስተዳደርን” ይሆናል።

በ”ዘይተቐልዐ ታሪክ ህዝቢ ኢሮብ” ዶክመንታሪ ፊልም ውስጥ ዛሬ በኢሮብ ወረዳ ተመስርቶ ስላለው የውስጥ አስተዳደር ዴሞክራሲያዊነት እንደሚከተለው ተነግሯል። እጠቅሷለሁ

”***<u>ህዝቢ ኢሮብ ተዛራቢ ቋንቋ ሳሆ ኮይኑ፣ እቲ ንዘበናት ተኸሊኡዎ ዝጸንሐ ምስ ባህሉን ቋንቋኡን ዝሳነ ፍሉይ ዓረሰ ምምሕድዳር ሎሚ ተመሊሱሉ ጽዋዕ ዴሞክራሲ ካብዝመዓጉ ብሄር ብሄረሰባት ሓደ ኢዩ”።</u>***

ወደ አማሪኛ ሲተረጎም <u>የኢሮብ ህዝብ የሳሆ ቋንቋ ተናጋሪ  ሆኖ፣ ዛሬ ለዘመናት ተነፍጎት የቆየው ከባህሉና ከቋንቋው ጋር የተዛመደ ልዩ የራሱ የውስጥ አስተዳደር ተመልሶለት የዴሞክራሲ ጽዋ ከተጎነጩ ብሄር ብሄረሰቦች አንዱ ነው</u> ይላል።

ዶክመንታሪ ፊልሙ ውስጥ ስለ ጥንቱ የኢሮብ ታሪክ በአብዛኛው ከአባቶቻችን በአፈታሪክ ደረጃ ሲነገረን የነበረው በምስል ተደግፎ በጥሩ ትግርኛ ተተርኳል። ለዚህም በክፍል አንድ መግቢያዬ ውስጥ ምስጋናየን አቅርቤአለሁ። የቅርብ ጊዜ ታሪካችንን በተመለከተ በተለይ ከ1966ቱ አብዮት ፍንዳታ በኋላ ያለውን የኢሮብ ህዝብ የተተረከው ታሪክ ግን ዶክመንታሪ ፊልሙ ታሪክን በታሪክነቱ የሚተርክ ሳይሆን የአንድ ድርጅት (የህወሓት) ፕሮፓጋንዳ አራማጅ የሚያስመስሉ አባባሎችን በተለያየ ቦታ በመጠቅም ይበልጥ ለህወሓት ፕሮፓጋንዳ ጥቅም ላይ ውለዋል ብል የተሳሳትኩ አይመስለኝም።

ምክንያቱም፣ አንደኛ፣ በህዝባዊ አብዮት የአፄ ኃይለስላሴ ንጉሣዊ አገዛዝ ተገርስሶ ወታደራዊ ደርግ በሀይል የህዝቡን የለውጥ እንቅስቃሴ በጉልበት ሲነጥቅ ወታዳራዊ አገዛዝን በትጥቅ ለመፋለም በ1967 ዓ.ም በዓሲምባና በደደቢት የትጥቅ ትግልን የጀመሩት ኢህአፓና ህወሓት በኢሮብ ውስጥ በተመሳሳይ ጊዜ (አንድ ወቅት) እኩል የትጥቅ ትግልን እንደጀመሩና ህዝቡም ከጅምሩ ጀምሮ ሁለቱንም ድርጅቶች እኩል እንዳስተናገዳቸውና እንዳቀፋቸው ተደርጎ

ቀርቧል። ሆኖም ግን ትረካው ከነበረው እውነት ጋር ፈጽሞ የማይገናኝ መሆኑ ብቻ ሳይሆን በወቅቱ በቦታው የነበረው እውነትንም የሚቃረን ነው።

ሁለተኛ፣ የኢሮብ ወረዳ ዋና ከተማ ከዓሊተና ወደ ዳውሃን የተቀየረበት መሰረታዊ ምክንያት የህወሓትና የሻዕቢያ አመራር ገና በረሃ እያሉ ባደረጉት ስምምነት መሰረት የተደረገ ድብቅ ዓላማ ያለው ጉዳይ ሆኖ ሳለ፣ ዶክመንታሪ ፊልሙ የኢሮብ ወረዳ ዋና ከተማ ከዓሊተና ወደ ዳውሃን የተቀየረበት ምክንያት ባጭሩ ዳውሃን ከዓሊተና የበለጠ ለትልቅና ዘመናዊ ከተማ ግንባታ የሚያመች ሰፊ ሜዳማ የሆነ ቦታ ስላላት ነው በማለት የህወሓትን ከንቱ ፕሮፓጋንዳን በመተረክ ሊያጃጅለን ይሞክራል።

ከዚህም አልፎ ዶክመንታሪ ፊልሙ ዛሬ በኢሮብ ውስጥ ያለው አስተዳደርን በተመለከተ ሃቁ በተቃራኒው መሆኑ በሁሉም ዘንድ እየታወቀ "የኢሮብ ህዝብ ከባህሉና ከቋንቋው ጋር የተዛመደ ዴሞክራሲያዊ የራስ አስተዳደር ተመስርቶለታል" በማለት ላሞኛቹህ ዓይናቹህን ጨፍኑ ሊለን ሞክሯል። ዶክመንታሪ ፊልሙ ውስጥ ስለ ኢሮብ ህዝብ "ዴሞክራሲያዊ የራስ አስተዳደር" የሚተረከው ከተለመደው የህወሓት ተራ ፕሮፓጋንዳ የዘለለ አይደለም። ፕሮፓጋንዳው የህወሓትን ተክለ-ሰውነት ለማሽሞንሞን በሚያመች መልኩ የተተረከ ፈጠራ እንጂ አንድ ዴሞክራሲያዊ የውስጥ አስተዳደር ማሟላት ያለበትን ቅድመ-ሁኔታዎችን ምን እንደሆኑ እንኳ ሳያመላክት እንዲሁ "የኢሮብ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ የራስ አስተዳደር መብት ተጎናጽፏል" በማለት ይሸመጥጣል።

<u>**እንደኔ እምነት አንድ ብሄረሰብ የተሟላ ዴሞክራሲያዊ የራሱ የውስጥ አስተዳደር አለው ለማለት የሚቻለው ብሄረሰቡ በራሱ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበረሰባዊ ጉዳዮች ላይ ያለ ማንም ጣልቃ ገቢነት ራሱ የአገሪቱ ህገመንግስት በሚፈቅደው መሰረት መወሰን ሲችል ነው።**</u>

ከዚህ የዴሞክራሲያዊ የውሰጥ አስተዳደር ፍች/ትርጉም አንጻር ዛሬ በኢሮብ ውስጥ የኢሮብ ህዝብ ምን ያህል የራሱ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበረሰባዊ ጉዳዮቹን ያለ ማንም ጣልቃ ገብነት እየወሰነ ነው? የሚለውን ጥያቄ ስናነሳ በዶክመንታሪ ፊልሙ ውስጥ እንደሚተረከው ሳይሆን ፈጽሞ በተቃራኒው ሆኖ እናገኘዋለን።

በርግጥ ዛሬ በኢሮብ ወረዳ የሚመደቡ የተለያዩ የአሰተዳደር ሰራተኞች በብዛት ከኢሮብ ህዝብ አብራክ የተወለዱ መሆናቸውን ልንክደው የማንችል ሃቅ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ እነዚህ የአሰተዳደር ሰራተኞች በዴሞክራሲያዊ መንገድ በህዝቡ የሚመረጡ ሳይሆኑ በገዢው ፓርቲ (በህወሓት) በምረጫ ሽፋን የሚመደቡ የፓርቲው ካድሬዎች ብቻ መሆናቸውም ሁሉም የሚያውቀው ፀሃይ የሞቀው ሃቅ ነው። የኢሮብ ህዝብ የተለያየ አመለካከት ያላቸው ተወዳዳሪዎች ያለምንም ተጽዕኖ ለውድድር ቀርበው፣ ህዝቡ ደግሞ ያለምንም ተጽዕኖ የሚፈልገውን የራሱን አመራር ለመምረጥ ሆነ ለመመደብ የሚችልበት ዕድል እስከዛሬ ፈጽሞ አላገኘም።

የኢሮብ ህዝብ ዶክመንታሪ ፊልሙ ውስጥ እንደሚተረከው የራሱ ውስጣዊ ፓለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበረሰባዊ ጉዳዮች ራሱ ወስኖ የዴሞክራሲን ጽዋ እየተጎነጨ ያለ ህዝብ ቢሆን ኖሮ፣ በኢሮብ ውስጥ ዛሬ የሚከተሉትን ለውጦች ማየት በቻልን ነበር፣

- ❖ ዛሬ እያየንና እየሰማን ያለነው የኢሮብ ወጣቶች ለተሻለ ኑሮና ስራ ፍለጋ አከባቢያቸውን እየለቀቁ ወደተለያየ አቅጣጫ የሚበታተኑበት ሁኔታ ሙሉ ለሙሉ ለመቅረፍ ባይቻለም የወጣቶቹ ስደት ካለፈው የሚቀንስበት ሁኔታ፣
- ❖ በአከባቢው ለወጣቶቹ የስራ ዕድል የሚፈጥርና ተስፋ የሚያሰጥ ሁኔታ ተመቻችቶ ወጣቶች በቀያቸው በሰላም እየሰሩ የሚኖርበት ሁኔታ፣
- ❖ በአከባቢው ሊሰሩ፣ ፕሮጀክቶችን ማጥናትና መመስረት ይችሉ የነበሩ ወጣት ምሁራን በአከባቢያቸው ህዝባቸውን ለማገልገል ፈቃደኛ የሚሆኑበት ሁኔታ ተፈጥሮ አቶ አለማ ተስፋይ Irob regions natural resources and potential for development በሚል ርእስ በእንግልዝኛ በጻፈው መጣጥፉ ውስጥ ያመላከታቸው በኢሮብ መሬት ከርስ የሚገኙ የተለያዩ ንጥረ ነገሮች በጥቅም ላይ ውለው የህዝቡንና የአከባቢውን ተፈጥሮአዊ ሁኔታ የሚቀይሩበት መልካም አጋጣሚን የሚፈጥር ሁኔታን የማየት መልካም አጋጣሚ፣
- ❖ በደርግ ፋሽስታዊ ስርዓት አገዛዝ ምክንያትም ሆነ ዛሬ ባለው የህወሓት ብቸኛ አምባገነናዊ አገዛዝ ምክንያት የተሰደዱ ወገኖች ወደ ቀያቸው በመመለስ ህብረተሰባቸውን በተለያየ መንገድ የሚያገለግሉበትን ሁኔታ፣
- ❖ እስከ ዛሬ ድረስ በሻዕቢያ ተጠልፈው ከ12 ዓመት በላይ ደብዛቸው የጠፋው ከ100 በላይ የኢሮብ ተወላጅ ኢትዮጵያዊያን ዜጎች ትክክለኛ ሁኔታና መዳረሻ ለማወቅ የምንችልበት ሁኔታን መፈጠር፣
- ❖ ውድ ልጆቹና በርካታ ኢትዮጵያዊያን ህይወታቸውን የገበሩለት ከአንድ ሶስተኛ በላይ የኢሮብ መሬት ከጥንት ከጥዋቱ የኢትዮጵያ መሆኑ የሚታወቅ ቢሆንም መሬቱ በአቶ መለስና ቡድናቸው ያለ ህዝቡ እውቅናና ፍቃዱ ለሻዕቢያ ማስረከብን የመሳሳሉ አሠራሮች ተወግደው የኢትዮጵያና የዜጎቿ ጥቅም ተከብሮ ማየት እንችል ነበር።

ዘይተቸልዐ ታሪክ ህዝቢ ኢሮብ "<u>ዛሬ ለዘመናት ተነፍጎት የቆየው ከባህሉና ከቋንቋው ጋር የተዛመደ ልዩ የራሱ የውስጥ አስተዳደር ተመልሶለት የዴሞክራሲ ጽዋ ከተጎነጩ ብሄር ብሄረሰቦች አንዱ ነው"</u> የሚለን በኢሮብ መሬት የሚኖረው ህዝባችን ዛሬ ከምንጊዜም በላይ በህወሓት ብቸኛ ቁጥጥር ስር ወድቆ ህልውናው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተገዘገዘ ወደ መጥፋት እያዘገመ ያለበ አሳዛኝ ሁኔታ ውስጥ የሚገኝ ህዝብ እየታወቀ እንደሆነ ግንዛቤ የሚያሻው ጉዳይ ነው።

"ዘይተቸዐ ታሪክ..." ዛሬ የራሱ የውስጥ አስተዳደር ተመልሶለት የዴሞክራሲ ጽዋ እየተጎነጨ ነው ብሎ የሚተርክለት የኢሮብ ህዝብ የሚገኝበት ተጫባጭ ሁኔታ ሲገመገም ሁኔታ እንደሚከተለው ሆኖ ነው የምናገኘው።

- ➢ በአከባቢው ለመኖር ተስፋ አጥ ሆነው አከባቢውን ለመልቀቅ የተገደዱ ሽማግሌዎች አከባቢውን እየለቀቁ ወደተለያዩ ከተሞች በመፍለስ አከባቢው መካሪ ሽማግሌ አልባ የሆነበት፣
- ➢ በአከባቢው ለመኖር ተስፋ የሚሰጥ ነገር በማጣት ስራ አጥ የሆኑ በርካታ ወጣቶች ስራ ፍለጋ ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ህይወታቸውን ከፍተኛ አደጋ ውስጥ በማስገባት አከባቢውን ለቀው እየፈለሱ ያሉበት ሁኔታን፣ሌሎችም ቁጥራቸው በውል የማይታወቁ

ወጣቶች በአከባቢው በሰፈነው አምባገነናዊ አገዛዝ ተማረው ወደተለያየ አቅጣጫ እየኮበለሉ ያሉበት ሁኔታ፣

- ቁጥራቸው በውል የማይታወቁ ወጣቶች በተለይ ሴቶች የቀሳፊው ኤች አይ ቪ ኤይድስ በሽተኞች የሆኑበት ሁኔታ ላይ መገኘታችን፤
- ከምንጊዜም ባለይ ባህላችንና እምነታችን እየተሸረሸረ በመሄድ ላይ መገኘቱን፤
- በተለያየ ጊዜ ብረት በታጠቁ መለዮ ለባሽና በመንግሥቱ የፀጥታ ሃይሎች የተለያዩ ወጣቶች በግፍ እየተደበደቡ/እየተገደሉም ያሉበት ሁኔታ ላይ መሆናችን…..ወዘተ. ነው የምናየው።

ባጭሩ በቦታው ያለው ነባራዊ ሁኔታ በ"ዘይተቐልዐ ታሪክ..." ላይ እንደሚተረክልን ሳይሆን የኢሮብ ህዝብ በአንድ ፓርቲ (በህወሓት) አምባገነናዊ አገዘዝ ስር እንደ ሌላው የኢትዮድያ ህዝብ እየተረገጠ ያለህዝብ መሆኑን ነው የሚያሳየው። በተለይ የኢሮብ ብሄረሰብ እንደ ብሄረሰብ የመቀጠል ሁኔታን ጠለቅ ብለን ስንመለከት ደግሞ ሁኔታው አሁን ባለበት ከቀጠለ የኢሮብ ብሄረሰብ እንደ አንድ ብሄረሰብ ህልውናው ከምንጊዜም በላይ አደጋ ውስጥ የገባበት ወቅት ላይ ነው የምንገኘው ቢባል ስሕተት አይሆንም። ስለሆነም ለ"ዘይተቐልዐ ታሪክ…."፣ **<u>ዛሬ ለዘመናት ተነፍጎት የቆየው ከባህሉና ከቋንቋው ጋር የተዛመደ ልዩ የራሱ የውስጥ አስተዳደር ተመልሶለት የዴሞክራሲ ጽዋ ከተጎነጩ ብሄር ብሄረሰቦች አንዱ ነው</u>** ለሚለው አተራረክ በቦታው ያለውን ታሪካዊ ሃቅ የሚተርክ ታሪክ ሳይሆን እየተተረከ ያለው የተለመደው የህወሓት አመራር የፈጠራ ፕሮፓጋንዳ ነው እላለሁ።

በመጨረሻም የዛሬውን መጣጥፌን ከመዝጋቴ በፊት ለሁሉም የኢሮብ ብሄረሰብ አባላት በያላችሁበት የሚከተለውን አጭርና ግልጽ መልእክት ለማስተላለፍ እወዳለሁ።

1. ነገሩ ጅብ ከሄደ ውሻ ጮኸ እንዳይሆንብን ሁላችን ኢሮቦች ታሪካችን እንደዚህ ተበርዞ ለድርጅት ፕሮፓጋንዳ መጠቀሚያ ሲሆን አንድ ላይ ሆነን ይህ አይሆንም ማለት መቻል አለብን።
2. በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ዛሬ በኢሮብ ህዝብ ህልውና ላይ በተፈጥሮና በሰው ሰራሽ ችግሮች ምክንያት እየደረሰ ያለውን የህልውና ማጣት አደጋ ማስቀረት ከሁሉም በፊት አስቀድመን ሁላችን ኢሮቦች ያሉብንን ጥቃቅን የማይረቡ ልዩነቶችና ቁርሾችን ለጊዜው ለይደር አሳድረን የኢሮብ ብሄረሰብ ህልውናን ለማሰቀጠል መተባበር መቻል አለብን እላለሁ።

ከኔ ጋር ለሚደረግ ግኑኝነት፣ beyene@yahoo.com መጠቀም ይቻላል።